# የአሲምባ ውይይት መድረክ
# ለፍኖተ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ራዲዮ
# ልዩ የዕርዳታ ዝግጅት ያደርጋል
# ቅዳሜ ኅዳር 26 ቀን 2013
# December 5, 2020

---

## ቅዳሜ ኅዳር 26 ቀን 2013
### December 5, 2020

**የፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ድምፅ ራዲዮ ጣቢያን እንርዳ፡-**

የኢሲምባ የፓለቶክ ውይይት መድረክ ቅዳሜ ኅዳር 26 ቀን 2013 (እኤአ 12/05/2020) ከቀኑ 2:00 የዋሽንግተን ዲሲ ሰዓት አቆጣጠር ጀምሮ የገንዘብ እርዳታ ለማሰባሰብ በምናደርገው ዝግጅት ላይ በውጭ ያላችሁ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እንድትገኙልን በማክበር እንጋብዛለን።

የፍኖተ ራዲዮ ጣቢያ ለኢትዮጵያውያን፣ በኢትዮጵያውያን፣ ስለኢትዮጵያውያን የተቋቋመና፤ ከተመሠረተበትም ጊዜ አንስቶ በሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እርዳታ ብቻ ፕሮግራሙን የቀጠለ ዕውነተኛ ኢትዮጵያዊ አማራጭ ራዲዮ ስለሆነ የሀገር ወዳዶችን እርዳታ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ይሻል።

በተለይም በአሁኑ ጊዜ በውጪ ያሉ የተቃዋሚ ኃይሎች ይዘውሯቸው የነበሩ በርካታ የሕዝብ መገናኛዎች በመደመር ስም ያለው መንግሥት ወዶ ገባ አገልጋዮች በሆኑበት ወቅት በጣት ከሚቆጠሩ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ የዜና አገልግሎት ሰጪዎች መካከል ፍኖተ ዋነኛው እውነተኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ ስለሆነ ዕርዳታችን ያስፈልጋዋል። ሕዝቡ የተዋደቀለት ትግል አቅጣጫውን ስቶ በዘረኝነት ተተብትቦ አደጋ ሊያደርስ የሚችል ኃይል ሆኖ እንዲወጣ የሚገፋፉትንና ለክሽፈቱ ሌት ተቀን የሚሠሩ አሰፍስፈው የሚወራጩትን የዘረኞች መንጋ ሴራቸውን በትምህርት ለማክሸፍ ይህ ራዲዮ ጣቢያ ሊጫወት የሚችለውን ሚና ከዝግጅቱ የምንገነዘብ ሁላ የአሁኑ ወጣት ለጋ ኃይል ኢትዮጵያዊ መልክና ቅርጽ እንዲይዝ የሚያስችል ጉልበትና ማስተማሪያ አስተማማኝ ኢትዮጵያዊ ራዲዮ ጣቢያችንን ካለማመንታት ተሰባስበን እንርዳ።

በዚህ ዕለት ከራዲዮ ጣቢያው፣ ከፍኖተ ርዕይ የዝግጅት ክፍልና ከኢሕአፓ የአመራር አባላት በመድረካችን በመገኘት አሁን ያለውን ያገራችንን ፖለቲካ ሁናቴ ላይና ስለ ራዲዮ ጣቢያው ገለጻ ስለሚያደርጉ፣ በመድረካችን በመገኘት ያላችሁን ጥያቄ በማቅረብ ወደፊትም ራዲዮኑ እንዴት ሊጠናከር

እደሚቻል ጠቃሚ ሃሳብ ልታቀርቡ የምችሉበት ሁናቴ ያመቻቸን ሲሆን፣ ከራዲዮ ዝግጅት ክፍሉ ጋርም በመተባበር ለዕለቱ ልዮ ዝግጅት ይዘን የምንቀርብ መሆኑን እናስታውቃለን።

የአሲምባ የፓልቶክ የውይይት መድረክ በየሳምንቱ ቅዳሜ በዋሺንግተን ዲሲ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 2 ሰዓት ጀምሮ የሚከፈትና እነሆ ለለፉት 14 ዓመታት የሀገራችንን ፖለቲካ ሁኔታ በሚመለከት የተለያዩ በሳል ሀሳቦች የሚንሸረሸሩበት ዴሞክራሲያዊ የውይይት መድረክ ነው።

የአሲምባ ውይይት መድረክ